# አገልጋዩን ለአገልግሎቱ

«ለጠቢብ ሰው ትምህርትን ስጠው፥ ጥበብንም ያበዛል፤ ጻድቅንም አስተምረው፥ እውቀትንም ያበዛል» (ምሳሌ 9፡9)።

1995 ዓ.ም

በወንጌላዊ አበበ ብርሃኑ
ከአቃቂ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

አሳታሚ:-

የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ

የፖ.ሣ.ቁ. 127፣ አዲስ አበባ

የመጀመሪያው እትም - 1995 ዓ.ም

2ኛው እትም (ከተጨማሪ ምዕራፍ ጋር) - 1998 ዓ.ም

The Servant for His Service

Printed by SIM Press

# መግቢያ

በክርስትና ዙሪያ ትልቅ ስፍራ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች አንዱና ዋናው አገልግሎት ነው። ይሁን እንጂ ከጊዜ ወደ ጊዜ በዚህ ትልቅ ጉዳይ ዙሪያ በርካታ ችግሮች ይስተዋላሉ። ምክንያቶቹን በጥሞና ለመመርመር ብንነሣ ከዋነኞቹ አንዱ በጣም ያወቅን መስሎን ተገቢውን አክብሮት ለአገልግሎት አለመስጠት ሊሆን ሲችል፥ ይኸውም የአገልግሎትን ምንነት ያለመረዳት ሌላው ችግር ይመስለኛል።

በአገልግሎት ዙሪያ አንዣብቦ ያለውን ይህን ዓይነቱን ችግር በጥቂቱ እንኳ ለመቅረፍ እያንዳንዱ አገልጋይ እግዚአብሔር በሰጠው ኃይልና ጸጋ የድርሻውን የመጣር አደራ አለበት። እኔም ይህ ሸክም ስለተሰማኝና የድርሻዬን እንድጥር የጌታ መንፈስ ስላነሣሣኝ በተለያዩ ጊዜያት በግልም ይሁን በጋራ በጌታ ፊት በሆንኩባቸው ዘመናት እርሱ በልቤ ያስቀመጠውን መንፈሳዊ ዘር አውጥቼ ለመዝራት ይህን የሥልጠና ትምህርት ለማዘጋጀት ጌታ የረዳኝ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ።

ይህ ለአገልግሎት የሚጋብዝ የሥልጠና ትምህርት ቀለል ባለ መልክ ለአሠልጣኝም ሆነ ለሠልጣኝ መሠረታዊ የሆነውን የአገልግሎት አሳብ ለማቀበል በሚያመችና ለውጤትም በሚያነሣሣ መልኩ ብቻ ለማቅረብ መጠነኛ ትኩረት ተሰጥቶበታል።

ይህ ትምህርታዊ ሥልጠና ሥልጠናውን ለሚወስዱና ለሚያሠለጥኑ አቅጣጫ ጠቋሚ እንጂ ፍጹምና የመጨረሻው አለመሆኑ እሙን ነው። በርእሶቹ ዙሪያ አሳቦቹን ማስፋት ቢቻልም የአዘጋጁ ዓላማ ስላልሆነ በዚህ መልክ ብቻ ለማቅረብ ተቆጥቤያለሁ።

ለምሳሌ፤ አንድ ተደናቂ የሳይንስ ምሁር በግኝቱ የተደነቁበት ሰዎች ኧረ ለመሆኑ እንዲህ ያለውን አስደናቂ ግኝት እንዴት ልታገኝ ቻልክ? ቢሉት «እኔ ይህን አስደናቂ ግኝት ያየሁት ከእኔ በፊት በነበሩት ሳይንቲስቶች ትከሻ ላይ ሆኜ ነው» አለ ይባላል።

የዚህ ትምህርታዊ ሥልጠና አዘጋጅ አባባልም ይኸው ነው። ይህ ትምህርት ከዚህ ቀደም ስለ አገልግሎት ያስተማሩት፥ የጻፉትና የተናገሩት ሁሉ አስተዋጽኦ ውጤት መሆኑን በመግለጽ ይህችን በይዘቷ ትንሽ በመልእክቷ ታላቅ እንደሆነች የማምንባትን ጽሑፍ ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ሳበረክት ታላቅ ደስታ እየተሰማኝ ነው።

ትርጉም፦ አገልጋዩን ለአገልግሎቱ የሚለው ርእስ ትርጉም

1. አገልጋይ የሚሆነውን አማኝ ለጌታ ሥራ ማዘጋጀትን ገላጭ ሲሆን፥

2. አገልጋይ የሚሆነውን አማኝ በውስጡ ለተቀመጠው የአገልግሎት ጸጋ ማዘጋጀት (ማነሣሣትን) ገላጭ ርእስ ነው።

<u>ዓላማው፡—</u>

የዚህ ትምህርታዊ ሥልጠና ዓላማዎች በጥቂቱ የሚከተሉት ናቸው፡—

1. ወደ አገልግሎት ለመግባት የሚመጣውን አማኝ ስለ አገልግሎት መጠነኛ ግንዛቤ ኖሮት እንዲሰማራ መርዳት፥

2. ለአገልግሎት ከሚመጡ የሚጠበቁ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረታዊ ነጥቦችን ማሳየትና ለውጤታማ አገልጋይነት ማነሣሣት፥

3. በተጨማሪ በአገልግሎት ሂደት ላይ የሚገኘውን አገልጋይ ይበልጥ ለመነሣሣትና ከትጋት ወደ ኋላ የቀረውን አገልጋይ ለማንቃት ነው።

በእነዚህ ዓላማዎች አማካኝነት ታማኝና እውነተኛ ደቀ መዛሙርትን እና ለጌታ ጠቃሚ አገልጋዮችን ለቤተ ክርስቲያን ለማስናዳት ነው።

እንደሚታወቀው ዓላማዎች ሁሉ ለግብ የሚበቁት በታሰበው ጉዳይ ውስጥ ተፈላጊ የሆነው አካል ሲገኝ ብቻ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጸው እግዚአብሔር አምላክ ለራሱ ሕዝብ ትልቅ ዓላማ አለው። ለዚህም ትልቁ መሣሪያው (ዕቃው) አገልጋዩ መሆኑን መረዳት አያስቸግርም።

በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር በየዘመኑ ሰው የመፈለግ አሳቡ አልተገታም። ሁላችንም እንደምናውቀው በዓለማችን ላይ ዘመን በጨመረ ቁጥር የሰው አስፈላጊነት እያነሰ የመምጣቱ ምክንያት የቴክኖሎጂው ማደግና ሥራዎች በማሽን እየተተኩ መምጣታቸው ሊሆን ይችላል።

# ማውጫ

መሪ ጥቅስ፦ «. . . መከሩስ ብዙ ነው ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው. . . » (ማቴ. 9፡37)


መግቢያ ገጽ

ትምህርት 1: ..................................................................

ክፍል 1:- አገልግሎት ማለት ምን ማለት ነው? ................ 1

ክፍል 2:- አገልጋይ ማለት ምን ማለት ነው? ........................ 4

ትምህርት 2:- የአገልግሎት መሠረት.................................. 8

ትምህርት 3:- የአገልግሎት ምክንያት..........................................15

ትምህርት 4:- የአገልግሎት ዓላማ ............................................21

ትምህርት 5:- የአገልግሎት ምሳሌ.............................................26

ትምህርት 6:- የአገልግሎት መሣሪያዎች..................................33

ክፍል 1: ጸሎት........................................................................34

ክፍል 2: የእግዚአብሔር ቃል ..............................................37

ክፍል 3: መንፈስ ቅዱስ ........................................................41

ትምህርት 7:- የአገልግሎት ዋጋ ...............................................46

ትምህርት 8:- የአገልግሎት ደረጃ (መጠን)...............................52

ትምህርት 9:- የአገልጋይ ችግሮች...........................................59

ትምህርት 10:- አገልጋይና ጊዜው............................................65


ከእነዚህ በተጨማሪ ለሠልጣኞቹ በክፍል ሥልጠና ወቅት የቤት ሥራዎችና ልዩ ልዩ ሙከራዎች /ጥያቄዎች/ መስጠት አገልጋዩን ስለ አገልግሎት ትጋት ጠያቂነት ግንዛቤ መስጪያ ተጨማሪ መንገዶች ናቸው።

«የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፥ እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል፥ የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል።» (ዮሐንስ 12፡26)

«. . . ፍሬ የሚያፈራውንም አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል» (ዮሐንስ 15፡2)

# ምስጋና

ከሁሉ በማስቀደም የእርሱን የከበረ አሳብ በእኔ በደካማው ውስጥ አሳድሮና አሳድጎ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጥቅምና ለእርሱም ክብር ይሆን ዘንድ ቸርነቱን ላሳየኝ አምላክ ክብርና ምስጋና ማቅረብ እወዳለሁ!

ይህ ጽሑፍ ለዚህ እንዲበቃ በልዩ ልዩ መንገድ ድጋፋቸውን ከቸሩኝ መካከል በመልካም አሳቦችና በምክር፥ በጸሎትም ከጎኔ ለቆመችውና ለደገፈችኝ ባለቤቴ ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ጌታሁን፥ እንዲሁም ከግሎብ ሥነ ጽሑፍ ጸሐፊ እኅት አልማዝ ወርቁን፥ በተለይ ጽሑፉን ኤዲት በማድረግና አስፈላጊውን ጥረት ከሁሉ አንጻር በማድረግ የደከሙትን ወ/ም ዘነበ ገ/ሃናን፥ በተጨማሪም ለዚሁ መሳካት የተባበሩትን ሚ/ር ፍሬድ ሚክጊንሊንና ባለቤታቸውን፥ ሚ/ር ጄምስ ቢኮክስንና ባለቤታቸውን፥ መጋቢ ገ/እግዚአብሔር ካህሳይና ባለቤታቸውን፥ ኢ/ር ወርቁ መኮንንንና ባለቤታቸውን፥ አቶ መርጊያ ሰርቤሳንና ባለቤታቸውን፥ አቶ መልካሙ ደርብንና ባለቤታቸውን፥ አቶ ዘለቀ ገለቱንና ባለቤታቸውን፥ ከሕይወት ሥነ ጽሑፍ ወ/ም አዲሴ አማዶን፥ የሌዊ አገልግሎት አገልጋዮችንም ከልብ አመሰግናቸዋለሁ።

በተጨማሪም ገና ጽሑፉን ከአነሣሱ ጀምሮ በታይፕ ሆነ በኮምፒውተር ደጋግሞ በመጻፍ ጽሑፉን በመሥራት የደከሙልኝን የአቃቂ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ጸሐፊ እኅት አስቴር ጋረደውን፥ የጓደኛዬ ወንጌላዊ ተገኔ ባለቤት እኅት ፀሐይ ዮናታንን፥ እኅት ዓለም ፀሐይ እውነቱን፥ የኤስ አይ ኤም ማተሚያ ቤት ኃላፊዎችንና ሠራተኞችን ሁሉ ከልብ ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

በመጨረሻም ከውድ ጊዜያቸው ቀርሰው አስተያየታቸውን በመስጠት ያበረታቱኝን ስማቸው በጽሑፉ በስተመጨረሻ የተጠቀሱትን አገልጋዮች ጌታ አገልግሎታችሁን ይባርክላችሁ ለማለት እወዳለሁ።

እንዲሁም የአቃቂ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን፥ አገልጋዮችንና መላውን ምእመን ይህን ጽሑፍ ለማሳደግ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳደረጉልኝ ስለማምን ከነፍሴ አመሰግናቸዋለሁ።

# ትምህርት አንድ

## ክፍል አንድ

# አገልግሎት ማለት ምን ማለት ነው?

ዓላማ፡- ወደ አገልግሎት ለሚመጣው አማኝ የአገልግሎትንና የአገልጋይን መሠረታዊ ትርጉም ለማመላከት ነው።

መግቢያ፡-

በዘመናችን ትክክለኛ ትርጉማቸውን ተረድተንና ተከትለን ካልተጠቀምንባቸው ዐቢይ ጉዳዮች አንዱ አገልግሎት ይመስለኛል። ምናልባትም እንኳ ስለ አገልግሎት አውቄአለሁ ለማለት ብንደፍርም መዘመርን፥ መስበክን፥ ማስተናገድን፥ ወዘተ... እንደ አገልግሎት ብቸኛ ትርጉም ተገንዝበን ይሆናል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳችንን በጥሩ ጥንቃቄ ስናጠና የምንማረው አገልግሎት ከእነዚህ ከምንረዳቸው ያለፈ ትርጉም ያለው መሆኑን ነው።

«ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ፥ የማትነቃነቁም፥ የጌታም ሥራ ሁልጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ።» (1ኛ ቆሮ. 15፡58)። በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ መሠረት የአገልግሎትን ምንነት መጠነኛ ግንዛቤ ለመጨበጥ እንሞክራለን። ከጥቅሱ ስንነሣ ደግሞ አገልግሎት ማለት በጥቅሉ <u>የጌታ ሥራ ማለት ነው</u>።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የጌታ ሥራ ማለት ይህ ማለት ብቻ አይደለም በሚል አሳብ ዙሪያ እንድንጀምር እወዳለሁ።

ስለዚህ፡-

1. የጌታ ሥራ ስንል ምን ማለታችን አይደለም?

   1.1 ዕለታዊ እንጀራችንን ለማግኘት ብቻ ብለን የምንሠራው ሥራ ማለት አይደለም።

   1.2 ሰዎች ስላዘዙን ብቻ ብለን የምናከናውነው ሥራ ማለት አይደለም።

   1.3 መርሐ ግብር ፕሮግራም ለመፈጸምና ለማስፈጸም ያህል ብቻ የምንሠራው ሥራ ማለት አይደለም።

እነዚህ ከላይ ያነሣናቸው ነጥቦች በአገልግሎት ዙሪያ ምንም ስፍራ የላቸውም ለማለት ሳይሆን ለእነዚህ ብቻ ብለን የምንንቀሳቀስበት ሁኔታ አይደለም ለማለት ነው።

ታዲያስ፡-

2. አገልግሎት (የጌታ ሥራ) ስንል ምን ማለታችን ነው?

2.1 የጌታ ሥራ ከእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት የተነሣ ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉት እንዲሠሩት የተሰጠ መንፈሳዊ ሥራ (ስጦታ) ነው።

አገልግሎት የእግዚአብሔር ምሕረትና ጸጋ እንጂ የማንነታችን ውጤት አይደለም። ይህ ሲገባን የጊዜያችንን፥ የጉልበታችንን፥ የእውቀታችንን፥ የገንዘባችንን አቅም አቀናጅተን በየትኛውም ጊዜና ቦታ ለጌታ ክብር የምንቀሳቀስበት መስክ (ሁኔታ) ነው። በ2ኛ ቆሮ. 4፡1 «ስለዚህ ምክንያት ምሕረት እንደተሰጠን መጠን ይህ አገልግሎት ስላለን አንታክትም።» ይላል።

- አገልግሎቱን (ሥራውን) እኔ ያገኘሁት በምሕረት ምክንያት ብቻ መሆኑን ስለተረዳሁ እኔ አልቆጠብም፥ ተስፋ አልቆርጥም ማለቱ ነው።

- የእግዚአብሔር ምሕረት ምን ያህል እንደበዛልን በተረዳን መጠን ነው መሆን የሚገባንን የምንሆነው። አገልግሎት ለአማኞች የተመቻቸ ድንቅ መንፈሳዊ ዕድል ነው።

2.2 የጌታ ሥራ (አገልግሎት) ማለት በቅዱሳን በጎ ፈቃደኝነት ላይ ተመሥርቶ የሚሠራ መንፈሳዊ ተግባር ነው።

«ዛሬ በፈቃዱ ራሱን ለእግዚአብሔር የሚቀድስ ማን ነው? (1ኛ ዜና 29፡5)። አገልግሎት በውስጣችን ባለው ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ አነሣሽነት እንጂ በማንም ግፊትና ጉትጎታ የምንሳተፍበት ጉዳይ አይደለም። ተለምነንና በሌሎች ተገፋፍተን ለማገልገል ከከጀልን እንኳ ጌታን ሳይሆን የምናስደስተው ምናልባት ሰዎችን ሊሆን ይችላል። ስለዚህ በፍጹም በጎ ፈቃደኝነት ከውስጣችን ፈንቅሎ በወጣ መንፈሳዊ አሳብ ተገፋፍተን እንድናገለግል ጌታ ይርዳን!

2.3 የጌታ ሥራ (አገልግሎት) ስንል ቅዱሳን እንዲባረኩ ብቻ ብለው ሳይሆን ስለተባረኩ የሚፈጽሙት ቅዱስ ተግባር ነው።

- አንዳንድ አማኞች ለምን እንደሚያገለግሉ ሲጠየቁ ለመባረክ እንደሆነ ይናገራሉ። መሆን ያለበት በእርግጥ እንድንባረክ ነው

ወይ? ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን በላከው መልእክቱ እንዲህ ብሏል። «በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።» (ኤፌ. 1፡3)። ይህ ጥቅስ እንኳ የሚያስገነዝበን በውስጣችን እግዚአብሔር ካስቀመጠው ድንቅ ጸጋ የተነሣ እንጂ ገና ለገና የሆነ ነገር ተስፋ አድርገን እንደምናገለግል አይጠቁመንም።

- ወደ አንድ የሥራ መስክ የምንገባው ለሥራው ብቃት በውስጣችን ስላለ እንጂ ዋጋ ስለምናገኝ አይደለም። በውስጣችን ባለው ብቃት ተገቢ ውጤት ካሳየን ደመወዛችንን ወይም ዋጋችንን እንከፈላለን የአገልግሎቱ ብቃት ደግሞ እግዚአብሔር በውስጣችን ያስቀመጠው ጸጋው ነው እርሱ ትልቅና ነፃ በረከት ነው።

አገልግሎት የተባረኩ አማኞች የመባረካቸው መግለጫ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ነው።

2.4 የጌታ ሥራ /አገልግሎት/ ስንል የአገልግሎቱ ባለቤት ታማኝ አድርጎ በቆጠራቸው ቅዱሳን ላይ ጌታ ያኖረው ውድና ክቡር መንፈሳዊ አደራ ነው።

«...መልካሙን አደራ በእኛ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ጠብቅ...» (2ኛ ጢሞ. 1፡14)

አደራ አንድ ቀን በሰጠን አካል የምንጠየቀው ሐብት ነው። አትርፈንበትም ቢሆን አክስረንበት ለባለቤቱ በመጨረሻ ሪፖርታችንን እናቀርብበታለን።

❖ ይህን አደራ በጸሎት፥ በማስተማር፥ በማስተናገድ፥ በዝማሬ፥ ወዘተ. . . በሰዎች መካከል ልንፈጽመው እንችላለን።

በአጠቃላይ፡-

❖ አገልግሎት ስንል የጌታ ሥራ ማለታችን ነው።

❖ አገልግሎት ስንል አገልጋዩ ተልዕኮውን የሚፈጽምበትና ጸጋውን ለሌሎች የሚያስተላልፍበት መንገድ ማለታችን ነው።

❖ አገልግሎት እነዚህን በሚመስሉ ሌሎች ነጥቦችን ሊተረጎም የሚችል መሆኑን እንረዳለን፥

ለመንደርደሪያ በሚሆን መልኩ ግን ይህን ያህል ካልን ይበቃናል።

# ትምህርት አንድ

## ክፍል ሁለት

## 3. አገልጋይ ማለት ምን ማለት ነው?

መግቢያ፡- ቀደም ብለን ባየነው ነጥብ መሠረት በዚህም ዙሪያ ትክክለኛውን ትርጉም የመረዳትና የማስረዳት ችግር ይስተዋላል። ለአንዳንዶቻችን አገልጋይነት እራስን ከሌላው አግንኖ የማቅረብ ነገር ሲንጸባረቅብን ለአብዛኞቻችን ጌታ ለምን፥ እንዴት፥ ለየት፥ ለማን እንደጠራን ያለማወቅ ውጤቶች ሲታዩብንም ይስተዋላል። ስለዚህ ይህን ለማረምም ሆነ ለማስቀረት ከአገልጋይ አኳያ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያመለክተንን እንማማራለን።

አገልጋይ ማለት፡- ጥሬ ቃሉ በአማርኛ መዝገበ ቃላት አንጻር ሲታይ ትርጓሜው ባሪያ፥ ታዛዥ፥ አሽከር፥ ጠቃሚ የሚሉትን ትርጉሞች ይይዛል። ነገር ግን ይህን አሳብ ወደ ጎን ሳንተው በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አባባልስ እንዴት ልንረዳው እንችላለን?

3.1 አገልጋይ ስንል በእግዚአብሔር የተመረጠና በጌታ መንፈሳዊ ሥራ ላይ የተወከለ መንፈሳዊ ሰው ማለት ነው።

«እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም. . . ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ...» (ዮሐ. 15፡16)

ኤር. 1፡1፤ ማር. 3፡13-15፤ ማቴ.25፡1፤ 12፡18-21 የመሳሰሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ በአገልጋይነት ዙሪያ ሊሆን ስለሚችል መመረጥ (መወከል) ጥሩ ግንዛቤ ይሰጡናል።

በእርግጥ በተመረጥንበት (በተወከልንበት) ታምኖ ወይም ስቶ የመገኘቱ ጉዳይ ለእኛ የሚተው ነው የሚሆነው።

2ኛ ዜና 29፡11 ይመልከቱ።

ማሳሰቢያ፡-

ስለ አገልጋይ ምርጫ ስናነሣ መረዳት የሚገባን ሰዎች በልዩ ልዩ ሁኔታዎች ወደ አገልግሎት ብቅ ሊሉ መቻላቸውን ነው።

ሀ. በእግዚአብሔር ፈቃድና ምርጫ (ኤር. 1፡4-11)

አብዛኞቹ አገልጋዮች በጌታ ፈቃድ ብቻ ወደ አገልግሎት የሚወጡ መሆኑ ግልጽ ነው።

❖ ራስህን ብቻ ለማገልገል እንጂ እግዚአብሔርን ለማገልገል አትፍራ!

ለ. አልፎ አልፎ በሰዎች ፈቃድ በወገንኝነት ሰዎች ሰዎቻቸውን በአገልግሎት ስፍራ ሊሰይሙ ይችላሉ ብሎ ማመን ስሕተት አይመስለኝም (ገላ. 1፡1)

- ጳውሎስ በዚህ ጥቅስ መሠረት ወዶ በሰው ፈቃድ አልመጣሁም ማለቱን እንረዳለን።

ሐ. አንዳንዶችም በራሳቸው ፈቃድ (ምርጫ) እራሳቸውን የሚሰይሙ ሰዎችም አይጠፉም «እንዲሁም ከራሳቸው አመንጭተው እየተናገሩ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው የሚሉትን ነቢያት እቃወማለሁ።» (ኤር. 23፡31) እንደሚለው የጌታ ቃል በራስ ምርጫና ፈቃድ አገልጋይ መሆንም አለ።

❖ በማን ጥሪ እየተንቀሳቀስኩ ነው? ብሎ መጠየቅ ብልህነት ነው።

3.2 አገልጋይ ስንል የእግዚአብሔር አሳብ፥ ዓላማ፥ ፕሮግራም የሚከናወንበት መጠቀሚያ ዕቃ ማለት ነው። (የሐዋ. 9፡15/፤ 22፡14 ይመልከቱ።)

- አገልጋይ እግዚአብሔር እራሱን ለሰዎች የሚገልጥበት መሣሪያም ነው።

በዚህ ዘመን ከምንሰማቸው ትልቅ የዋህነት አልያም ሞኝነት ሊባል የሚችል አባባል አገልጋዩ «ጌታን እንጂ እኔን አትዩኝ» የሚለው ቃሉ ነው።

በእርግጥ ጌታን ደብቀን እራሳችንን ለማሳየት ጥረትና ትግል ማድረግ አይኖርብንም። ነገር ግን ጌታ ምንነቱን በእኛ ለማሳየት እኛ የፕሮግራሙ ማስተላለፊያ መስመር እንድንሆነው አስቦ እንደመረጠን መዘንጋት አይኖርብንም።

<u>ለምሳሌ</u>፥ ቴክኖሎጂው ያፈራልንን ስለ ኮምፒውተር ስንገነዘብ ሁለት ትላልቅ ዋና ክፍሎች እንዳሉት በተለይ ባለሙያዎቹ ጠንቅቀው ያውቃሉ።

ኮምፒውተርን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ልናየው እንችላለን ስንል አንዱ ክፍል ሀርድዌር በመባል የሚታወቀው ሲሆን፥ ይህ ክፍል የሚገልጸው ውጫዊ ገጽታውን ሲሆን፥ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ሶፍትዌር በመባል የሚታወቀው ውስጣዊ ገጽታውን ነው። ማንኛውም በሶፍትዌሩ ያለው ፕሮግራም የሚታየው በሀርድዌሩ የመሆኑን ያህል፥ አገልጋይ የእግዚአብሔር ፕሮግራም ማለትም እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሊገልጠው የሚፈልገው ማንኛውም ጉዳይ የሚገለጥበት ወይም የእግዚአብሔር ፕሮግራም የሚተላለፍበት መሣሪያ ነው።

❖ የእግዚአብሔር ቅንነት፥ ፍቅር፥ ምሕረት፥ ርኅራኄ ወዘተ... የመሳሰሉት ፕሮግራሞቹ የሚተላለፉት ወይም የሚተያዩት በአገልጋዩ ሕይወትና አገልግሎት ስለሆነ አትዩኝ ማለት ምን ማለት ነው?

3.3 አገልጋይ ስንል ጌታው ለእርሱ የከፈለውን መሥዋዕትነትና ውለታ አስቦ ጌታ የሚያዘውን በታማኝነት ለመታዘዝ የተሾመ ማለት ነው።

- ጌታው የሚለውን ወይም የሚያሳየውን በታማኝነት ሊያከናውን የተሾመ ማለት ነው። «የካህኑም የአሮን ልጅ አልዓዛር በመብራቱ ዘይት በጣፋጩም ዕጣን ላይ ሁልጊዜ በሚቀርበው በእህሉ ቁርባንና በቅባቱ ዘይት ላይ ይሾም...።» (ዘኁ. 4፡16፤ 1ኛ ጢሞ.1፡12 ይመልከቱ።)

- አገልጋይ ስንል ሰዎች ከመንፈሳዊ አንጻር የሚኖርባቸውን ሸክም፥ ድካም፥ ጉድለት፥ ወዘተ... ለመርዳትና ለመደገፍ ባለ አደራ የሆነ ሰው ማለት ነው።

«እኛም ኃይለኞች የሆን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንንም ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል።» (ሮሜ 15፡1)

«ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም።» (ገላ. 6፡2)

3.4 አገልጋይ ስንል በጌታ ቤት ወይም በቅዱሳን መካከል የጌታ ሥራ እንዳይቀዘቅዝና እንዳያቋርጥ የተቻለውንና ተገቢውን ጥረት አድራጊ የጌታ ባርያ ማለት ይቻላል።

- በእግዚአብሔር ቤት መንፈሳዊ ነገር (እንቅስቃሴ) እንዳይዳፈን ከአገልጋይ የተሻለ መሣሪያ የለም።

«በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በምስክሩ ታቦት ፊት ባለው መጋረጃ ውጭ አሮንና ልጆቹ ከማታ እስከ ማለዳ ድረስ በእግዚአብሔር ፊት እንዲበራ ያሰናዱት፤ ...» (ዘፀ. 2፡21)

(1ኛ ሳሙ. 3፡3 ይመልከቱ።)

ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሥራ በቅዱሳን መካከል ከቀዘቀዘ የሚከተሉት ክፉ ክስተቶች ሊከሰቱ ይችላሉ።

❖ ራእይ ይጠፋል

❖ በሰዎች ሕይወት ያለመርካት ይፈጠራል

❖ ሁኔታዎች ይጨልማሉ

❖ የሰዎች ወደ ጌታ የመምጣት እንቅስቃሴ ይቀዘቅዛል፥ ብሎም ይቋረጣል።

❖ አማኞች ኃጢአትን በቀላሉ ለመለማመድ ይደፍራሉ።

ይህ ሁሉ ክስተት እየሆነና የጌታም ሥራ እየቀዘቀዘም እንኳ ቢሆን ፕሮግራሞች ግን ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ሊካሄዱ ይችላሉ።

ማጠቃለያ፡- ዛሬ ስንቶቻችን ነን የአገልግሎትንና የአገልጋይነትን ትርጉም በትክክል ተረድተን የምናገለግለው?

በተለይ አገልጋይ ወደ አገልግሎት ፊጥኖ ከመሮጥ ይልቅ (በፊት) የአገልግሎትንና የአገልጋይነትን ምንነት የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረውና እንደሚያዘው መረዳትን ተቀዳሚ ተግባሩ ማድረግ የሚጠበቅበት ሲሆን፥ በትክክለኛው አገልግሎትና አገልጋይነት ውስጥ እየተመላለሰ ማገልገልም ይገባዋል።

አገልጋይነት፡- አገልጋይነት ነው!!!

«...የእስራኤልን ልጆች ለማገልገል የሚያስፈልገውንም ነገር ይጠብቁ።» (ዘኍ. 3፡8)

# የትምህርት አንድ

## የሙከራ (የመወያያ) ጥያቄዎች

«... ነገር ግን አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ይበረታሉ፥ ያደርጋሉም» (ዳን. 11፡32)።

1. አገልግሎት ምን ማለት አይደለም?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

2. አገልግሎት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ነው የተረዳኸው?

_______________________________________________

_______________________________________________

3. አገልጋይ ማለት ምን ማለት ነው?

4. ሰዎች ወደ አገልግሎት እንዴት ሊመጡ ይችላሉ?

5. ከትምህርት አንድ የተረዳኸውን እውነት ግለጽ (አስረዳ)።

# ትምህርት ሁለት

# የአገልግሎት መሠረት

ዓላማ፡- በአገልግሎት መስክ የሚሰማራው አገልጋይ ከመነሻው በሕይወቱ ተለውጦ ማገልገልን እንዲያተኩር ለመርዳት ነው።

መግቢያ፡-

ማንኛውም ጉዳይ መነሻ ወይም መሠረት ሊኖረው ግድ ነው። ምክንያቱም መሠረት የሌለው አልያም መሠረቱ ያልተስተካከለ ነገር ሁሉ ዘለቄታነቱ አስተማማኝ ሊሆን ስለማይችል ነው።

- እግዚአብሔርም የከበረ ሥራውን በከበረ መሣሪያ ማከናወን ያምናል።

እንደ ሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 6፡47–49 አገላለጽ፥ መሠረት ማለት ምን ያህል ጊዜን ጥንቃቄንና ጥሩ ክትትልን የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ለመሠረቱ ጥሩ ትኩረት ከተሰጠበት ቀጣዩ ቀላልና ቀልጣፋ ሆኖ ሊከናወን ይችላል። በአንጻሩም መሠረቱ ከተበላሸ ሁሌም እንዳዘኑና እንደተጎዱ መኖር ይሆናል። አገልግሎትንም በጥንቃቄ ስናጤነው መሠረት ያለውና ሊኖረው የተገባ ስለመሆኑ እንገነዘባለን።

የአንድ አገልግሎት መሠረት ምንድን ነው ብለን እናምናለን? ማንኛውም ወደ አገልግሎት ሊመጣ የሚወድ ክርስቲያን የአገልግሎትን መሠረት የተረዳና በዚያም መሠረት ላይ የቆመ መሆን ይኖርበታል።

ወደ መልሱ ስንመለስ፡– የአንድ አገልግሎት ትክክለኛ መሠረት መሆን የሚችለው በአገልጋዩ ሕይወት መታየት የሚችለው መንፈሳዊ ለውጡ፥ ወይም (የአገልጋዩ የተለወጠ ሕይወት ነው።)

ቤተ ክርስቲያን በተቻለ መጠን ሁሉ አገልጋዮቿ ከተለወጠ ሕይወታቸው የተነሣ እያገለገሉ ለመሆኑና ላለመሆኑ በጽኑ ማሰብ ይኖርባታል፥ ይህ ብቻም ሳይሆን ተለውጦ ከማገልገል አኳያ አቋሟ ፍጹም ጠንካራ ሊሆን ይገባል። ያለዚያ ብዙ ዓለማዊነት ያልተላቀቃቸውን አገልጋዮች አቅፋ የዓለማዊነት ጠረን ያለው አገልግሎት በውስጧ ሊበራከትና ልትቸገር ትችላለች። ካልተለወጡ ሰዎች በሚመጣ አገልግሎት ሌሎች የተለወጡ ሰዎችን ማፍራት ከቶ የማይሞከር መሆኑን ልብ እንበል።

ባለፉትም ጊዜያት እንኳ እንደተገነዘብነው ጥቂቶች ሳይለወጡ የተለወጡ እያስመሰሉ በቤተ ክርስቲያናችን የአገልግሎት መጠለያ ገብተው አገልግሎቷንና ተገልጋዮቿን የጎዱ አይታጡም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ መረሳት የሌለበት ለውጥ ሂደታዊ እንጂ ቅጽበታዊ ያለመሆኑን ነው።

ለውጥ አንዳንዶች እንደሚሉት አባ ጨጓሬ በሂደት ወደ ቢራቢሮነት የሚለወጥበትን ዓይነት እንቅስቃሴ ሊሆን ስለሚችል፥ ሰዎችን ወደ አገልግሎት ስናመጣቸው በለውጥ ሂደት እንዲያልፉ እንርዳቸው እንጂ ሰዎችን በመጠራጠር ብቻ በፍርሃት መመልከት አይኖርብንም ለማለት እወዳለሁ።

## የተለወጠ ሕይወት በመንፈሳዊ ክልል አነጋገር፡-

- ❖ በመሠረቱ ለውጥ ማለት ከምንም በላይ በክርስቶስ ሰዎችን የማዳን ዓላማ ውስጥ ማለፍ መቻል ወይም ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ በእምነት ከመቀበል የሚጀምር ጉዳይ ነው።
- ❖ ዋናው አሳቡን ሳይለቅ ለውጥን በተለያየ ዓይነት አገላለጽ መመልከት ደግሞ ይቻላል።

በመንፈሳዊ ክልል የተለወጠ ሕይወት ለአገልጋይነት ትልቅ ግምት የሚሰጠው ነው። የተለወጠ ሕይወት ስንል ምን ማለታችን ነው?

1. የተለወጠ ሕይወት ስንል ከጌታ ጋር በእርግጥ የተገናኘ ሕይወት ማለታችን ነው። (የሐዋ. 9፡1 ይመልከቱ።)

   - ለውጥ የውስጥ መንፈሳዊ እድሳትን ማግኘት ማለት ነው!!!
   - የተለወጠ ሕይወት ሊታይብን የሚችለው መንፈሳዊነት የሚስተዋልብን ጌታ በተገናኘን ጊዜ ብቻ መሆኑ እሙንም ነው።
   - ለውጥ ከጌታ ጋር ከተገናኘንበት ቅጽበት ጀምሮ በውስጣችን ሊከሰት የሚችል ድንቅ ክስተት ነው፥ ክስተቱ ደግሞ በአማኙም ሆነ በአገልጋዩ ውስጥ የአዕምሮ፥ የፈቃድ፥ የስሜት፥ የእምነት ለውጥ ማምጣት (ማስከተል) የሚችል ነው።
   - የአገልጋይ በአዕምሮ (በእውቀት) ማደጉ ከሚረጋገጥባቸው መንገዶች በጥቂቱ፡-

     1.1 አገልጋዩ ወደ አዲስ ሕይወቱ ከመምጣቱ በፊት በምን ዓይነት ሕይወትና ሁኔታ እንደተመላለሰ ማወቁ ነው። (1ኛ ጢ.ሞ. 1፡13-17 ይመልከቱ)።

- ሐዋርያው ጳውሎስ የሕይወቱን ለውጥና ከመንፈሳዊ አንጻር ያገኘውን ታላቅ ግንዛቤ የሚያስጨብጠው የትናንቱን ማንነቱን በማሳሰብ (በማሳየት) ነው። ክርስቶስ ሳይገናኘው በፊት ምን ዓይነት አስጸያፊ ሕይወትና ባሕርይ እንደነበረው መረዳቱን፥ ይህም የለውጡ ጠቋሚም ነው። በእርግጥ ጌታ ነክቶት (ተገናኝቶት) የማይለወጥ አይኖርም።
- ታዲያ ዛሬ ስንቶቻችን በተሻለ ሕይወት እየተመላለስንና እያገለገልን መሆኑን በመረዳት የትናንቱን ክፉ ሕይወት ግን ለሌሎች ልንጠቅሰው ምን ያህል ይታሰበናል (ይታወሰናል)?

1.2 አገልጋዩ አሁን በምን ዓይነት ሕይወትና ሁኔታ እየተመላለሰ መሆኑን በማወቁ የለውጥ እድገቱን ማሳወቅ መቻል ነው። (ሮሜ 5፡1–5፤ 8፡35–39 ይመልከቱ)።

- ❖ አገልጋይ ለውን እንዴት ሆኖ እያገለገለ እንዳለ ስለዛሬው ሕይወቱ ልክ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ማወቅ ይኖርበታል፤
- ❖ ለውጥ ማለትም አገልጋዩ በሚኖርበት ዘመን እግዚአብሔር አምላኩን በማወቅና በመፍራት ውስጥ አልፎ መኖርና ማገልገል መቻል መሆኑንም ነው የምንገነዘበው።
- ❖ የሐዋርያው የመንፈሳዊ መረዳቱ ለውጥ እድገትና ለዚህ ሕይወት እንዴት እንደኖረ በቀላሉ መማር እንችላለን።

1.3 አገልጋዩ ወደፊት ምን ሊጠብቀው እንደሚችልና ለዚያ ሕይወት እንዴት እንደሚኖር አስቦ መመላለሱን በማወቁ ነው። 2ኛ ጢሞ.1፡12፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡5–8 ይመልከቱ። በዚህ ደግሞ ክርስቶስ የአገልጋዩን ሕይወት ብቻ ሳይሆን ተስፋውን ሁሉ ሳይቀር እንደለወጡለት መመልከት ይቻላል።

- ❖ እነዚህ ከላይ ያየናቸው ነጥቦች የመንፈሳዊ እውቀት (የአእምሮ) እድገት ለውጥ ማረጋገጫ ብቻ ሳይሆኑ የአገልጋዩ መንፈሳዊ ሕይወቱም ለውጥ ማረጋገጫም ናቸው።

2. የተለወጠ ሕይወት ስንል ቀድሞ ለኃጢአት ከነበረው ስሜቱ የተላቀቀ ሕይወት ማለታችን ነው።

   - ❖ ለውጥ በውጭ የሚታየውን ዓለማዊነት መጋፋትና መጋፈጥ መቻል ነው።
   - ❖ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች እንደሚስማሙበት በተለይ ስሜታችን እንዱ የለውጣችን ማረጋገጫ መሆኑን ነው።

ማለትም ትናንት ላይ ስለ ኃጢአት ድርጊቶች የነበረን ስሜትና ዛሬ ስለ ኃጢአት የሚሰማን ስሜት የት ላይ እንዳለን ስሜታችን ምስክር ሊሆነን ይችላል። ትናንት በኃጢአት ይደሰት የነበረው ስሜታችን ዛሬ ያዝንና ይጸጸት ጀምሯል ወይ?

«የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው መጽናናትን ያገኛሉ።» (ማቴ. 5፡4)

የዚህ ጥቅስ አሳብ ወይም ኀዘኑ ምን ዓይነት ሊሆን እንደሚችል በቀላሉ መረዳት የሚቻል ይመስለኛል።

ጽድቅ በዓመጽ ሲሸፈን፥ እውነት ስትረገጥና መንፈስ ቅዱስ በነገሮች ሁሉ ሲያዝን አብሮ የማዘንንና ስሜታችን አብሮ የመጎዳቱን ጉዳይ የሚተረጉም መሆኑን እምናለሁ።

- ውስጡ (ስሜቱ) ተለውጦ የሚያገለግል አገልጋይ (ሮሜ 12፥3 ይመልከቱ።)

1. በአገልግሎቱ ባለቤት ዘንድ ደስታን የሚፈጥር ሲሆን፥
2. በተገልጋዮቹም አእምሮ የተመቸ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል።

❖ ውድ አገልጋዮች ከጌታ በፊት የነበረን አጠቃላይ ስሜትና ዛሬስ ያለን አጠቃላይ ስሜት ምን ልዩነት እናስተውልበታለን? ትናንት በእኛ ላይ ሠልጥኖ የነበረውን ክፉ ዓለማዊ ድርጊት፥ ክፉ ማንነት፥ ክፉ ስሜት መከላከልና መዋጋት መቻል የመንፈሳዊ ለውጥ አንዱ ነጸብራቅ ነው።

❖ የትናንቱን አላስፈላጊ ነገር ሁሉ ማጥራት፥ ማስተካከል፥ ማስወገድ በራሱ የለውጣችን ሌላው ጠቋሚ ነው። በዘጸ. 25፥10 ላይ የምንመለከተው አሳብ ከዛፍ ዝርያዎች ጠማማ፥ አስቀያሚና እሾሃማ የሆነውን እንጨት እግዚአብሔር ስለ መመልከቱና ስለ መምረጡ ስንረዳ ታሪኩ ያስገርመናል። ማለትም ያ ጠማማ የግራር እንጨት በባለሙያው እጅ ተጠርቦና ተሠርቶ፥ ተውቦ፥ ስሙና መልኩ ተለውጦና በወርቅ ተለብጦ ታቦት ተብሎ ለመጠራት የመቻሉ ምሥጢር፥ እኛም በእግዚአብሔር እጅ ስንሆን የሕይወታችንና የመንፈሳችን ታሪክ ተለውጦ የትናንት ነገሮቻችን ተወግደው የጌታ የክብሩ መገለጫ እንድንሆን መሆኑን የሚያመላክተን ነው።

- መለወጥ ማለት ከአሮጌው አዳማዊ ባሕሪያችንና ሥራችን መላቀቅ የሚጠፋውንና የሚያጠፋውን ክፉ ምኞታችንን መለየት መቻል ነው። (ኤፌ. 4፥22፥ 23 ይመልከቱ።)

3. የተለወጠ ሕይወት ስንል በጌታው ፍቃድ ፍጹም ለመመራት የተሸነፈ ሕይወት ማለታችን ነው።

- በሰው ሕይወት ውስጥ ከእግዚአብሔር የመለወጥ ኃይል ውጪ ፈቃዱን በቀላሉ መሠረዝ እጅግ ከባድና አስቸጋሪ ጉዳይ መሆኑ ግልጽ ነው።

❖ ሐዋርያው ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ስለመሸነፉ ከሚያስረዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንዱ፡—

«እየተንቀጠቀጠና እየተደነቀ፡— ጌታ ሆይ፥ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? አለው» (የሐዋ. 9፡6 ይመልከቱ።)

ለውጥ በአንድ አገልጋይ ሕይወት ከሚረጋገጥበት መሥመር አንዱ የራስን ፈቃድ ወደ ጎን በመተው የጠራውን ጌታ ፈቃድ የማስተናገድ ልብ ሲስተዋልበት ነው። እርግጥ የጌታን ፈቃድ መከተልና መፈጸም በአብዛኛው ከባድ እንደሚሆንና ዋጋ እንደሚያስከፍል የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ እንደ አገልጋይ የጥሪያችን ትኩረት ፈቃዱን በመከተሉና በማድረጉ ላይ መሆን እንዳለበት ጥርጥር የለውም።

«እነሆ፥ አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ላደርግ መጥቻለሁ።» (ዕብ. 10፡9)

- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ መረዳትና ጽናትን የሚጠይቅ መሆኑን በጥቂት የአገልግሎት ዘመናችን ተገንዘብነው።

«የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችኋል።» (ዕብ. 10፡36)

- በእግዚአብሔር ፈቃድ ለመመላለስ መቻል የሕይወታችን ለውጥና ብስለት ማረጋገጫ ነው።

4. የተለወጠ ሕይወት ስንል በሌላው አንጻር ለቅድስናው ጠንቃቃ የሆነ ሕይወት ማለታችን ሊሆን ይችላል። (ዘሌ. 20፡26 ይመልከቱ።)

«ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፥ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና።» (ዕብ. 12፡14)

ቅድስና ማለት ምን ማለት ነው? ለሚለው መልስ ከሚሆኑት አንዱ የልብ ወይም የመንፈስ ጨዋነትን መላበስ መቻል ነው። ቅድስናን መለማመድ በተለይም በውስጥ ሕይወት ጨዋ ሆኖ መመላለስ ለአንድ የእግዚአብሔር ቤት አገልጋይ በየዕለቱ ከአገልግሎቱ ተቀዳሚ ባሕሪው መሆኑ በግልጽ መታወቅ ይኖርበታል።

ውድ ወገኖች፥ ቅድስናችንን ሳንጠብቅ አገልግሎት ብናበዛ የበደል ጉድለታችንን ሊሸፍንልን እንደማይችል በራእይ መጽሐፍ ውስጥ ከትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መማር ይቻላል። (ራእይ 2፡20—23 ይመልከቱ።) አገልጋይ ለቅድስና ጥንቁቅ ካልሆነና ውስጣዊ ጨዋነቱን ካልጠበቀ የሚያጎለው መንፈሳዊ ነገር ቀላል አይሆንም።

የእስራኤል ካህናት ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንደምንረዳው ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሲገቡ ምንም እንኳን በውጭ ገላቸውን ታጥበው፥ ንጹሕ የፀዳ ልብስ ተክህኖ ለብሰውና ሽቶ ተቀብተው መግባቱ የሥርዓታቸው አንዱ ቢሆንም ምናልባት ግን ከውስጥ ጨዋነት (ንጽሕና) ጉድለት የተነሣ ቅድስናቸውን ጥለው እግዚአብሔር ቢያገኛቸው ሊቀሰፉ ስለሚችሉ በእግራቸው ገመድ ታስሮ ወደ ቅድስት ይገቡ ነበር።

- ቅድስናውን ከማይጠብቅ አገልጋይ ጋር እግዚአብሔር ጠብ ሊኖረው ይችላል ማለት ነው።

«እናንተ የእግዚአብሔር ዕቃ የምትሸከሙ ሆይ፥ እልፍ በሉ፥...» (ኢሳ. 52፡11)

- ❖ በመሠረቱ ቅድስና በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ (ስንመራ) በውስጣችን ወይም በልባችን የሚፈጠር መንፈሳዊ ጨዋነት መሆኑን ደግሜ መጠቆም እወዳለሁ። በዘፀ. 39፡30 «... ቅድስና ለእግዚአብሔር...» የሚለውን የእስራኤል ካህናት ዓርማ በየዘመናቱ የምንገኝ አገልጋዮች ከውስጣችን ጀምሮ ከፍ አድርገን ልናሳየው በእግዚአብሔር የሚጠበቅ የመለወጣችን ምሥጢር መገለጫ መሆን ያለበት ጉዳይ ነው።
- ❖ አገልጋይ ምንም ያህል ካህን፥ ሌዋዊ ዛሬ ደግሞ፡- ዘማሪ፥ ሰባኪ፥ አስተማሪ፥ ወዘተ... ቢባልም ቅድስናውን ሳይጠብቅ ቢያገለግል ግን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አባባል ምናምንቴ ተብሎ ሊጠራ የግድ ይሆናል። (1ኛ ሳሙ. 2፡12 ይመልከቱ።)

አገልጋይ የንግግሩን፥ የአመለካከቱን፥ የድርጊቱንና የውበቱን እንኳ ቅድስና መጠበቅ ይጠበቅበታል!!

## ማጠቃለያ፡-

ውድ ወገኖች፥ ከጌታ በአደራ የተቀበልነውን አገልግሎታችንን በተለወጠ ሕይወት ጀምረን በተለወጠ ሕይወት አገልግለን፥ በተለወጠ ሕይወት መፈጸም አለብን። ከእኛ በፊት የነበሩት ቅዱሳን ባሪያዎቹ ሕይወታቸውን ጠብቀው በተለወጠ፥ በተስጠና በተቀደሰ ሁኔታ ስሜታቸውን እየገዙ ፈቃዳቸውን ለጌታ ፈቃድ እያስገዙ፥ በንጹሕ ሕሊና አገልግለው ማለፋቸውን ተገንዝበን፥ እኛም በተለወጠ መንፈስና ሕይወት ማገልገል እንደሚገባን በመጨረሻ ጫን የምንለው አሳብ ነው።

# ትምህርት ሦስት

# የአገልግሎት ምክንያት

<u>ዓላማ</u>፡- አማኙ በአገልግሎት ውስጥ ሲመላለስ የአገልግሎት ብቸኛ ምክንያት ስለሆነው ስለ ፍቅር ግንዛቤን ለማስጨበጥ ነው።

<u>መግቢያ</u>

ማንኛውም ሰው አንድን ነገር ለመፈጸም የሚነሣው በምክንያት ነው። ምክንያቶች ከአገልጋይ አገልጋይ ሊለያዩ እንደሚችሉ ይታመናል። እኛን ዛሬ ለአገልግሎት ያነሣሣን ምክንያት ምንድን ነው?

ስለ አገልግሎታችን ምክንያት መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስናጠና የምንገነዘበው ዋና ነገር ቢኖር የአገልግሎታችን ምክንያት መሆን ያለበት፤ በመለኮታዊ ፍቅር መነካት ብቻ እንደሆነ ነው!

- መለኮታዊ ፍቅር ስንል ከምንም ነገር ጋር ባልተያያዘ መልኩ የሆነ ፍቅር ለማለት ነው።
- ያለ ፍቅር ማገልገል ይቻላል ወይ የሚል ጥያቄ ሊፈጠር ይችላል። አዎን ያለ ፍቅር ማገልገል ይቻላል። <u>ለምሳሌ</u>፥ ነቢዩ ዮናስ ያገለገለው በነነዌ ሕዝብ ፍቅር አልነበረም፤ እግዚአብሔር የግድ ብሎት እንጂ። ዛሬም ሰዎች በራሳቸው ውስጥ ካሉ ልዩ ልዩ ምክንያቶቻቸው የተነሣ ብቻ ሊያገለግሉ ይችላሉ።

አንድ ሠራተኛ ወደ ሥራ ገበታው ሲገባ መታወቂያውን ይዞና የሠራተኛ ልብሱን ለብሶ የሚሠማራውን ያህል፥ አገልግሎት የጌታ ሥራ መሆኑንና አገልጋዩ ደግሞ ሠራተኛው እንደሆነ ባለፉት ትምህርቶች ውስጥ ማየታችን ይታወሳል።

<u>ምሳሌ</u>፤ በአንድ ሆስፒታል ውስጥ ከመግቢያው በር ጀምሮ እያንዳንዱን ሠራተኛ በልብሱ መለየት የሚቻለውን ያህል፤ ፍቅር በጌታ ሥራ ውስጥ የሠራተኛው ልብስ ወይም መለያው ነው፤ (ሮሜ 13፡8-10፤ 1ኛ ቆሮ. 13፡1፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡13-24 ይመልከቱ።)

❖ ደግሞም ያለ ልብስ የሚሄድ እብድ የመሆኑን ያህል፥ አገልጋዮችም መንፈሳዊ እብድት እንዳይስተዋልብን ፍቅርን እንልበስና እናገልግል የሚለውን ነው መልዕክቱ የሚመክረን።

«... በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት» (ቆላ. 3፡13፥ 14)።

«የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብና ከበጎ ሕሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው፤» (1ኛ ጢሞ. 1፡5-7)።

የመንፈሳዊው ሥራ ሠራተኞች መለያ (መታወቂያ) ሊሆን የሚችለው ፍቅር ብቻ ነው።

❖ በመሠረቱ ፍቅርን መተርጎም ከበድ ያለ ጉዳይ ቢሆንም፥ መጠነኛ ትርጉሙን ያመለክቱን ዘንድ የሚከተሉትን እናነሣለን።

በተለይ ፍቅርን ከአገልጋይ አኳያ፡-

1. ፍቅር በሌላው አካል (ወገን) ስሜት ውስጥ ለማለፍ የሚደረግ የፈቃደኝነት እንቅስቃሴ ማረጋገጫ ነው።

   ❖ ሌላው ወገን ሲያዝን አብሮ የማዘን ስሜት

   ❖ ሌላው ወገን ሲደሰት አብሮ የመደሰት ስሜት የፍቅራችን ነጸብራቅ ከሆኑት ጥቂቶች ናቸው።

2. ፍቅር ከሌላው አካል (ወገን) ጋር በጋራ ለመኖር፥ ለማገልገል ስንል የምንከፍለው፥ የምናሳየው መሥዋዕትነት ማረጋገጫ ነው።

ክርስቶስ ስለ ፍቅር ያሳየውን መሥዋዕትነት ከምንማርባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በዋናነት እነዚህን ይመልከቱ፤ (ፊልጵ. 2፡5፤ ዮሐ. 1፡14)። እኛም ከሌሎች ጋር ለማገልገል ከፍቅር አንጻር ምን ይስተዋልብናል?

3. ፍቅር ለሌላው አካል (ወገን) ያለንን በጎ አመለካከት፥ ርኅራኄና አክብሮት የምንመሰክርበት የተግባር እንቅስቃሴ ማረጋገጫ ነው (ሉቃስ 10፡27 ይመልከቱ።) ከደጉ ሳምራዊ ሕይወት የምንማረው ይህን ትልቅ ጉዳይ ነው።

4. ፍቅር በተለይ የምናገለግለው ወገን ያለ አግባብ ጉድለት፥ ድካም፥ ያለአገባብ የሆነን አካሄድ ሁሉ ለማረምና ለማቅናት የሚደረግ ፍጹም ግልጽነት የሞላበት እንቅስቃሴ ነው። (ቆላ. 1፡28ን ይመልከቱ።)

ይህ አሳብ ጠንካራ ምክርን፥ ተግሣጽን ጠቋሚ ነው።

- ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ ከሚለው አምላካዊ ትእዛዝ መገንዘብ ካለብን አንዱ፥ ሌላው ወገናችን ተሳስቶ ስናገኘው መገሠጽ፥ ስሕተቱን መጠቆም በንጹሕነትና በቅንነት እስከሆነ ድረስ አስፈላጊነቱ ታላቅ ነው፤ (ዕብ. 12፡6-11፤ 2ኛ ተሰሎ. 3፡15 ይመልከቱ።)

ጳውሎስም «በብዙ መከራና ከልብ ጭንቀት በብዙ እንባ ጽፌላችሁ ነበርና ይህም እናንተን አብዝቼ የምወድበትን ፍቅር እንድታውቁ እንጂ እንዳሳዝናችሁ አይደለም፤» (2ኛ ቆሮ. 2፥4) ይላል።

ሐዋርያው ለቆሮንቶስ አማኞች ምን ያህል ከባድ መልእክቶችንና ተግሣፆችን እንዳስተላለፈ እናስታውሳለን። ነገር ግን ከፍቅር የተነሣ ብቻ ነበር የሚለው በዚህ ጥቅስ መሠረት።

- አገልጋይ በፍቅር መገሠጽም ይገባዋል!!
- በፍቅር መገሠጽንም መቀበል ይገባዋል!!
- መጽሐፍ ቅዱሳችን የፍቅራችንን ቅደም ተከተሉንም ያስገነዝበናል።

1. አገልጋይ ከሁሉ አስቀድሞ የአገልግሎቱ ባለቤት በሆነው በአምላኩ በእግዚአብሔር ፍቅር መነካትን የመጀመሪያ ምክንያቱ አድርጎ ማገልገል ይኖርበታል (ዘዳ. 6፥5)። ጌታ አምላክህን በፍጹም ኃይልህ፥ ነፍስህ፥ አሳብህ፥ ውደድ. . . ። በዮሐንስ 21፥15 ላይ ጴጥሮስ ወደ አገልግሎት ከመሰማራቱ በፊት የተጠየቀው «ትወደኛለህን» የሚል ነው። ዛሬም መንፈስ ቅዱስ እኛን እንዲሁ ይለናል።

አገልጋይ ሆይ፡-

- የምትወደኝ ከሆነ ግልገሎቼን መግብ
- የምትወደኝ ከሆነ ጠቦቶቼን ጠብቅ
- የምትወደኝ ከሆነ በጎቼን አሰማራ መባሉ ግድ ነው።

የአገልግሎት ፍቅር ኖሮን ከምንሮጠው ይልቅ በአምላካችን ፍቅር ተነክተን የምንሮጠው የአገልግሎት ሩጫ ውጤታማ ነው (ሮሜ 5፥5 ይመልከቱ።)

አገልጋይ እግዚአብሔር አምላኩን ከምንም ነገር አስበልጦ የሚወድ ሊሆን ይገባዋል፤ (መዝ. 132፥1)። የዚህን ጥቅስ ሙሉ አሳብ ስንረዳ ዳዊት ምን ያህል ለአምላኩ ፍቅር እንደነበረው በቀላሉ መማር ይቻላል።

ለምሳሌ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ

ሀ) በሮሜ 8፥35-39 ስለ ክርስቶስ የነበረውን ጥልቅ ፍቅር ይናገራል።

ለ) በ2ኛ ቆሮ. 5፡14–15 የሐዋርያው የአገልግሎቱ እንቅስቃሴ በክርስቶስ ፍቅር ምክንያት እንደነበር ይጠቁማል። ለክርስቶስ የመኖርንና የማገልገልን ፍቅር ምክንያት ያደርግ ነበር። ከዚህም የተነሣ እንዲህ ሲል ጽፎአል፡– «ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በማይጠፋ ፍቅር ለሚወዱ ሁሉ ጸጋ ይሁን፤» (ኤፌ. 6፡24)

❖ ዛሬም ወደ አገልግሎት ከመምጣታችን በፊት የአገልግሎቱን ባለቤት በማፍቀር መነካታችንን መፈተሽና ማረጋገጥ ይኖርብናል።

2. በአገልግሎታችን ተጠቃሚ በሆኑትና ባልሆኑት ሰዎች ፍቅር በመነካት ማገልገል ይኖርብናል፤ «ፍቅሬ በክርስቶስ ኢየሱስ ከሁላችሁ ጋር ነው፤» (1ኛ ቆሮ. 16፡24፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡7፥8 ይመልከቱ።)

በተለይም የምናገለግለውን መንጋ ማፍቀር ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው!

- ክርስቲያናዊ ፍቅር ማለት እግዚአብሔር እኛን በወደደበት ዓይነት ፍቅር ሌሎችን መውደድ መቻል ማለት መሆኑን አገልጋይ መገንዘብ አለበት (ያዕ. 2፡1–4 ይመልከቱ።)
- ከእኛ አሳብና አቋም ጋር የማይስማሙትን ጭምር ማፍቀር የአገልጋይ ሁሉ ድርሻ መሆኑን መዘንጋት የለበትም።
- ፍቅር የክርስቶስ ደቀ መዝሙር የመሆናችን መታወቂያ ነው (ዮሐ. 13፡35 ይመልከቱ።)

ወገኖች፥ በዮሐንስ 15፡8 ከምናገኘው ጥቅስ ልንማር የምንችለው ፍቅር ፍሬ ነው። የአገልግሎታችን በሮች ድመከፈት አንዱ ምክንያቱም ፍቅር መሆኑን ማመን አለብን፤ (ራእይ 3፡7 ይመልከቱ።)

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችን በማፍቀር ጉዳይ ላይ ሲያተኩር ባልንጀራህን ውደድ ይላል፤ ይህም ማለት፤ «. . . ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው» (ሉቃስ 10፡27)።

## 2.1 እንደ ራስ መውደድ

ለራስህ የምታስበውን፥ ለራስህ የምትጠነቀቀውን፥ ለራስህ የምትመኘውን ያህል ለባልንጀራህ እንዲሁ አድርግ ማለት ነው። ከ2ኛ ቆሮ. 2፡12 እንደምናየው ስለ ክርስቶስም ወንጌል ወደ ጢሮአዳ በመጣሁ <u>ጊዜ ለጌታ ሥራ በር ምንም ቢከፈትልኝ ወንድሜን ስላላገኘሁት መንፈሴ ዕረፍት አልነበረኝም፤</u> ነገር ግን ከእነርሱ ተሰናብቼ ወደ መቄዶንያ ወጣሁ ይላል። ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው

ከአገልግሎታችን በላይ በምናገለግላቸው ሰዎች ፍቅር ልንነካ የሚገባን መሆኑን ነው (2ኛ ቆሮ. 2፡4)።

- ፍቅር የሰዎችን ወደ መከራ መሮጥ አይቶ እራሱን አይደብቅም፤ በባልንጀራው አስቸጋሪ ሁኔታ ሁሉ እንኳ መካከል መግባት አይፈራም።

- በእውነተኛ ባልንጀርነት ውስጥ ሊኖር ስለሚገባው ፍቅር አገልጋይ ሊማር ከሚችልበት የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አንዱ ከ2ኛ ሳሙኤል 1፡25 ውስጥ በዳዊትና በዮናታን መካከል ስለነበረው ጤናማና ባልንጀራውን እንደ እራስ ስለመውደድ የተጻፈው ነው።

በተጨማሪም በቁጥር 17 «. . . ዳዊትም ለሳኦል ተቀኘለት» ከሚለው አሳብ የሚደነቅ ፍቅር መማር ይቻላል። ስለሚቃወሙን እንኳ ጉዳት ማዘን የአገልጋይነት ድርሻችን እንደሆነ ስንቶቻችን ነን የሚገባን?

2.2 እንደ ራስ ይቅር ማለት

ሁላችንም እንደምናውቀው የሰው ልጅ ራሱን ይቅር የማለት ጥሩ ልምድ አለው። በዚሁ መልክ ባልንጀራውን ይቅር ማለት ይጠበቅበታል። ፍቅር ደግሞ ብዙ ጨርቅ የማይሸፍነውን የባልንጀራውን ገመና ይሸፍናል። «. . . ይልቅ ተመልሳችሁ ይቅር ማለትና ማጽናናት ይገባችኋል፤» (2ኛ ቆሮ. 2፡7-11)።

በተለይ አገልጋይ ሰዎችን ይቅር በማለት ሕይወቱ መታወቅ አለበት፤ እርሱን ወይም እርሷን ይቅር ከምል እንዲህና እንዲያ ይሁንብኝ ማለት ፈጽሞ ከአገልጋይ የማይጠበቅ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል።

- ይቅርታ የፍቅር ውጤት ነው፤ ፍቅር ደግሞ ሁሉን ማሸነፊያ ነው። በ2ኛ ሳሙኤል 26፡13-21 ትልቁ አገልጋይ ዳዊት በፍቅር ምክንያት ሳኦልን በይቅርታ መንፈስ እንደተመለከተው የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል።

ዳዊትም ባሳየው የይቅርታ መንፈስ ምክንያት ሳኦልም «በድያለሁ ልጄ ተመለስ ዛሬ ነፍሴ በዓይንህ ፊት ከብራለችና ከዚህ በኋላ ክፉ አላደርግብህም እነሆ ስንፍና አድርጌአለሁና እጅግም ስቻለሁ፤» ብሎ ተጸጽቶአል።

- የጌታ አገልጋይ እስጢፋኖስ እየገደሉት ላሉት እንኳ ከፍቅር የተነሣ ይቅርታን እየማለደላቸው ሕይወቱ ማለፍዋን እናስብ (የሐዋ. 7፡60)። በተለይም አገልጋይ ጥላቻን እንደ

እግዚአብሔር ሰውነቱ የተጸየፈና አገልግሎትን ከሚጎዳ ነገር የራቀ ሊሆን ይገባዋል።

- የአገልጋዮች ክብራችን ባልንጀሮቻችንን በማክበርና በመውደድ ሊገለጥ ይችላልና ወደዚያ እናድላ፤ አጥብቀን እንከተለው ለማለት እወዳለሁ።

3. በተጠራንለትና በአደራ በተቀበልነው አገልግሎት ፍቅር በመነካት ማገልገል ይኖርብናል፤ ነህ. 6፡1–3 «. . . እኔም ትልቅ ሥራ እሠራለሁ እወርድ ዘንድ አይቻለኝም. . .»

«. . . የአሕዛብ ሐዋርያ እንደ መሆኔ መጠን አገልግሎቴን በትጋት እፈጽማለሁ።» (ሮሜ 11፡13)

- ሰው የሚወደውን ነገር ያከብራል፤ ለሚወደው ነገር ይጠነቀቃል፤ ለሚወደው ነገር ጊዜውንና ያለውን ሁሉ ይሰጣል። «ስለዚህ ምክንያት ምሕረት እንደ ተሰጠን መጠን ይህ አገልግሎት ስላለን አንታክትም» (2ኛ ቆሮ. 4፡1)፥ ያለው የሐዋርያው አባባል በአገልግሎት ዙሪያ የማይዘነጋ ነው።
- ለአገልግሎታችን ፍቅር አለን ማለት በምንም የማይለወጥ ሸክም አለን ማለት ነው።
- አገልግሎታችን የክርስቶስን ፍቅር አስበን የምናከናውነው የፍቅራችን ምላሽ፤ መግለጫና መሥዋዕትነት መሆኑን በመረዳት በፍቅር ማገልገል ይጠበቅብናል።
- በአገልግሎታችን ፍቅርና ራእይ የተጠመደ ከሆነ የአገልግሎታችን ጊዜ ማለት ለእኛ ለአገልጋዮቹ ብርቅ ነው (2ኛ ዜና 29፡20)። አገልጋይ የአገልግሎት ምሥጢር የገባው ከሆነ ጊዜውን በአልባሌና በምናምንቴ ጉዳይ አያባክንም።
- ይህ ሲገባን እንደ እኛ አሳብ የመሆንን ነገር እንጠላለን፥ ፀያፍ እናደርገዋለን። ለሠራልኝ ጌታ መሥራት አለብኝ ብለን በሁሉ ቆራጥ እንሆናለን (ራእይ 2፡26 ይመልከቱ።)

አገልግሎታችንን ካፈቀርን ጊዜያችንን፥ ጉልበታችንን፥ እውቀታችንን፥ ገንዘባችንን ሁሉ እንሰጣለን፥ እናቀርባለን።

<u>ማጠቃለያ</u>፡– አገልጋይ አገልግሎቱን የሚያከናውንበትን ምክንያት በተገቢው መልኩ በመረዳት አምላኩ ከምንም በላይ በሚያተኩርበት ባህርይ እየተሞላ ለአገልግሎቱ ባለቤት፥ ለአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች በውስጡ እግዚአብሔር ላስቀመጠው ጸጋ ልዩ ፍቅር ኖሮትና ይህንን ምክንያት አድርጎ በአደራው ዙሪያ እንደሚንቀሳቀስ ማስመስከር ይኖርበታል።